በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

# የአስር ቀን የአየር ሁኔታ

# ግምገማና ትንበያ መጽሔት

## ከጁላይ 21-31/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ

## እንዲሁም ከኦገስት 1-10 እና 11-20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ኦገስት 2024

አዲስ አበባ

ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

**ርዕስ** **ገፅ**


እ.ኤ.አ ከጁላይ 21 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ - 1 -

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከጁላይ 21 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ - 3 -

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከጁላይ 21 እስከ 31/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት - 3 -

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከጁላይ 21 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር - 3 -

እ.ኤ.አ ከጁላይ 21 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ - 4 -

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጁላይ 21 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ - 4 -

እ.ኤ.አ ከጁላይ 21 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ - 5 -

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከጁላይ 21 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ - 5 -

እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ - 6 -

ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከኦገስት 1-10, 2024 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ - 7 -

ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከኦገስት 1-10, 2024 የሚኖረዉ ከፍተኛ የዝናብ መጠን - 7 -

እ.ኤ.አ ከኦገስት 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ - 8 -

ካርታ 8 እ.ኤ.አ ከኦገስት 11-20_2024 የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ - 8 -

እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ - 9 -

እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ - 9 -




ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

# እ.ኤ.አ ከጁላይ 21 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ

ባለፉት አስራ አንድ ቀናት የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ጠንካራ እና የተሻለ የደመና ክምችት ነበራቸው፡፡ ከዚሁ ጋር በተያየዘም በመካከለኛው፣ ምስራቅ፤ በምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብ፣ በሰሜን እና በሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ አግኝተዋል፡፡ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው አከባቢዎች መካከል በባህርዳር 51.4፤ በጎንደር 42.4፤ በጎሬ 43.3፤ በሀሮማያ 48.0፤ በአማን 45.9፤ በአምባ ማሪያም 56.2 እና 44.2፤ በአርሲ ሮቤ 74.2፤ በአዋሽ አርባ 45.0፤ በአዴት 69.4፤ በባቲ 42.0፤ በብላቴ 42.1፤ በቡሌ ሆራ 40.0፤ በጭሮ 64.9፤ በዳሊፋጊ 40.6፤ በደብረ ብረሃን 57.0፣ በደብረ ታቦር 53.4 እና 45.6፤ በእንዋሪ 118.2፤ በጋምቤላ 75.6፤ በግምቢ 58.9፤ በጊዳ አያና 78.3፣ በጃራ 50.8 እና 45.7፤ በጅንካ 60.2 እና 55.3፤ በላሊበላ 86.0፤ በሊሙገነት 42.4፤ በማይጨዉ 40.5፣ በመሃልሜዳ 42.0፤ በአዳማ 63.8፤ በስንቃጣ 42.0፣ በሽሬ 62.5፤ በቴፒ 47.5፤ በባቱ 46.4፤ በግራዋ 49.5፤ በጉብሬ 43.6፤ በቁሉቢ 46.6፣ በላንጌ 56.0፣ በካራሚሌ 50.2 እንዲሁም በጨለንቆ 90.4 እና 47.9 በሚ.ሜ ይገኙበታል።


ባለፉት አስራ አንድ ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ፣ ምስራቅ፣ ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ እና ሰሜን ሸዋ(ሰላሌ)፣ ሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፣ ቡኖ በደሌ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ፣ ጅማ፣ ቄለም ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ ምስራቅ ባሌ፤ ከትግራይ ክልል የምስራቅ፣ የሰሜን ምዕራብ እና የምዕራብ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል ዋህግምራ፣ ሰሜን እና ደቡብ ወሎ፣ የኦሮሞ ብሄረሰብ ልዩ ዞን፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ጎጃም፣ ሰሜን፣ ማዕከላዊ፣ ደቡብ እና ምዕራብ ጎንደር፣ አዊ እና ሰሜን ሸዋ ዞኖች፤ ከሱማሌ ክልል ሲቲ፣ ኤረር እና ፋፋን ዞኖች፤ ከአፋር ክልል ቅልበቲ፣ ፈንቲ፣ አውሲ፣ ሀሪ እና ጋቢ ዞኖች፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል፣ አሶሳ፣ ካማሺ እና የማኦኮሞ ልዩ ዞን፤ ከጋምቤላ ክልል ኑዌር፣ አኝዋክ እና ማዣንግ ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጋሞ፣ ጎፋ፣ ወላይታ፣ ባስኬቶ እና ጌዲኦ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ስልጤ፣ ካምባታ፣ ሀዲያ፣ ሀላባ፣ ጉራጌ እና ምስራቅ ጉራጌ፣ የየም ልዩ ዞን፣ ማረቆ እና ጠምባሮ ዞኖች፤ ሁሉም የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ ከደቡብ




ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ፣ ኮንታ፣ ሸካ፣ ዳዉሮ፣ ምዕራብ ኦሞ እና ከፋ ዞኖች እና ድሬደዋ ላይ ከ61-300 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ6-10 ቀናት ያህል ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም ከኦሮሚያ ክልል ባሌ እና ጉጂ ዞኖች፤ ከትግራይ ክልል ማዕከላዊ ዞን፤ ከአፋር ክልል አውሲ ዞን፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል አማሮ፣ አሌ፣ ደራሼ፣ ኮንሶ እና ቡርጂ ዞኖች፤ ከጋምቤላ ክልል የኢታንግ ልዩ ዞን እንዲሁም አዲስ አበባ እና ሀረር ላይ ከ5-60 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ1-5 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2) ፡፡


ባለፉት አስራ አንድ ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከኦሮሚያ ክልል ጅማ፣ ኢሉባቦር፣ ሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ፣ ቄለም ወለጋ፣ ቡኖ በደሌ፣ ምስራቅ፣ ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ እና ሰሜን ሸዋ (ሰላሌ)፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ ዞኖች፤ አዲስ አበባ፤ ከትግራይ ክልል ምስራቅ፣ ማዕከላዊ፣ ደቡብ ምስራቅ፣ ሰሜን ምዕራብ እና ምዕራብ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል ሰሜን እና ደቡብ ወሎ፣ ዋህግምራ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ጎጃም፣ ሰሜን ሸዋ፣ ሰሜን፣ ማዕከላዊ፣ ደቡብ እና ምዕራብ ጎንዳር እንዲሁም አዊ ዞኖች፤ ከአፋር ክልል ቅልበቲ፣ ፈንቲ፣ አውሲ፣ ሀሪ እና ጋቢ ዞኖች፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል አሶሳ፣ መተከል፣ የማኦኮሞ ልዩ ዞን እና ካማሺ ዞኖች፤ ከጋምቤላ ክልል የኢታንግ ልዩ ዞን፣ ኑዌር፣ አኝዋክ እና ማዣንግ ዞኖች፤ ከሱማሌ ክልል ኤረር፣ ፋፋን እና ሲቲ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ እና ምስራቅ ጉራጌ፣ ሀላባ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ስልጤ እና የየም ልዩ ዞን፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ፣ ሸካ፣ ኮንታ፣ ከፋ እና ዳዉሮ ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ባስኬቶ፣ ጌዲኦ፣ ጎፋ፣ ጋሞ እና ወላይታ ዞኖች፤ ሀረር እና ድሬዳዋ ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ አግኝተዋል (ካርታ 3) ፡፡




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከጁላይ 21 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከጁላይ 21 እስከ 31/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት




ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከጁላይ 21 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር




ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

## ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

### እ.ኤ.አ ከጁላይ 21 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት አስራ አንድ ቀናት በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ ክፍሎች በመጠን የተስፋፋና ብዙ ቦታዎችን ያዳረሰ የእርጥበት ሁኔታ ነበራቸው፡፡ ይህም ሁኔታ ከኤፕሪል ጀምሮ ለተዘሩ እንደ በቆሎና ማሽላ ለመሳሰሉት የረጅም ጊዜ የመኸር ሰብሎች፤ ለተለያዩ ቋሚ ተክሎችና የጓሮ አትክልቶች የውኃ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም የክረምት ወቅታቸውን ጠብቀው ተዘርተው በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የመካከለኛ ጊዜ የመኸር ሰብሎች አዎንታዊ ሚና ነበረው። በተጨማሪም የተገኘው እርጥበት ዘግይተው ለሚዘሩ እንደ አጃ ለመሳሰሉ የአጭር ጊዜ ሰብሎች ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረው፡፡ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የአርብቶ አደርና የከፊል አርበቶ አደር አካባቢዎች ላይ የተገኘው እርጥበት የመጠጥ የውሃ እና የግጦሽ ሳር አቅርበትን ከማሻሻል አንጻር አዎንታዊ ሚና ነበረው፡፡ በአንፃሩ በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከነበረው ከባድና ተከታታይነት ካለው ዝናብ ጋር ተያይዞ የጎርፍና የመሬት መንሸራተት የነበረ ሲሆን፤ ይህም በሰው ህይወት በእንስሳት እና በሰብሎች ላይ ከፍተኛ የሆነ ጉዳት አድርሷል። በተለይም በጎፋ ዞን በገዜ ጎፋ ወረዳ፣ በመካከለኛው ሲዳማ ዞን በዎንሾ ወረዳ፣ በደቡብ ወሎ ዞን በደሴ ከተማ፣ በጅማ ዞን በጌራ ወረዳ፣ እንዲሁም በምዕራብ አርሲ በኮፈሌ ወረዳ ከፍተኛና ተከከታታይነት ካለው ዝናብ ጋር ተያይዞ የመሬት መንሸራተት በመከሰቱ በሰው፣ በእነስሳት፣ በሰብሎች እና በንብረት ላይ ከፍተኛ ጉዳት አድርሷል (ካርታ 4)፡፡





ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጁላይ 21 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከጁላይ 21 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት አስራ አንድ ቀናት በአብዛኛው አባይ፣ ተከዜ፣ አዋሽ፣ ባሮአኮቦ፣ ኦሞጊቤ፣ አፋር ደናክል፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ዋቤ ሸበሌ፣ ገናሌ ዳዋ እና የኦጋዴን ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ የእርጥበት መጠን አግኝተዋል፡፡ በተለይም የላይኛው ተከዜ፣ አፋር ደናክል እንዲሁም የላይኛው እና የመካከለኛ አባይ፣ በጥቂት የኦሞግቤ እና አዋሽ ተፋሰሶች ላይ እጅግ በጣም ከፍተኛ የሆን የእርጥበት መጠን አግኝተዋል። ይህም ሁኔታ የገጸ ምድርና የከርሰ ምድር ውኃን ከማሻሻል እንዲሁም የግድቦችን እና የወንዞች ውኃን መጠን ከማሳደግ አኳያ አዎንታዊ ሚና የነበረው ሲሆን፤ በተለይም በአንዳንድ ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ከባድ መጠን ያለው እርጥበት መኖሩን ተከትሎ ከወንዞች እና ከግድቦች ያለገደብ መሙላት ጋረ የተያያዘ ተጽዕኖ እንደነበረ መረጃዎች ያመለክታሉ (ካርታ 5)፡፡




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከጁላይ 21 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

በመደበኛ ሁኔታ በኦገስት የመጀመሪያዎቹ አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በአብዛኛዎቹ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በይበልጥ ይጠናከራሉ፡፡ በመሆኑም የክረምቱ ዝናብ በስርጭትም ሆነ በመጠን በተሻለ ሁኔታ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ ከፍተኛ ጥንካሬ የሚያሳይበት ጊዜ ነው፡፡

በመጪዎቹ አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በሁሉም የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ በተስፋፋና በተጠናከር ሁኔታ ቀጣይነት ይኖራቸዋል፡፡ በተለይም በምዕራብ፣ በሰሜን ምዕራብ፣ በሰሜን፣ በሰሜን ምስራቅና እና በመካከለኛዉ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ጠንካራ የዝናብ መጠንና ስርጭት እንደሚኖራቸው አሀዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ (ካርታ 6)፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች ላይ በመነሳት በምዕራብ፣ በሰሜንና በመካከለኛዉ የሀገሪቱ ስፍራዎች ላይ በ24 ሰዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖር አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 6 )፡፡ በመሆኑም ከሚኖረዉ ተደጋጋሚነት ካለዉ ከባድ መጠን ዝናብ ለወንዞች ሙላትና ለቅጽበታዊ ጎርፍ መከሰት እንዲሁም የመሬት መንሸራተት የማስከተል አቅም ስለሚኖረዉ ከወዲሁ ማህበረሰቡና የሚመለከታቸዉ አካላት አስፈላጊዉን ቅድመ ጥንቃቄና ዝግጅት ማድረግ እንደሚያስፈልግ የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት ይጠቁማል (ካርታ 6 እና 7) ፡፡


በአጠቃላይ በሚቀጥሉት አስር ቀናት ከትግራይ ክልል ምስራቅ፣ ማዕከላዊ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ምዕራብ እና ደቡብ ምስራቅ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል ሰሜን፣ ማዕከላዊ፣ ደቡብ እና ምዕራብ ጎንደር፣ ሰሜን፣ ምዕራብ እና ምስራቅ ጎጃም፣ ዋህግምራ፣ አዊ፣ ባህርዳር ዙሪያ፣ ሰሜን እና ደቡብ ወሎ፣ ሰሜን ሸዋ፣ የኦሮሞ ብሄረሰብ ልዩ ዞን፣ ከአፋር ክልል ቅልበቲ፣ ፈንቲ፣ ሃሪ፣ እና ጋቢ ዞኖች፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ እና ካማሺ ዞኖች፣ ከጋምቤላ ክልል ኑዌር፣ አኝዋክ፣ ማዣንግ እና የኢታንግ ልዩ ዞን፤ ከኦሮሚያ ክልል ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ ጅማ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ፣ ሆሮ ጉዱሩ፣ ቄለም ወለጋ፣ ሰሜን ሸዋ (ሰላሌ)፣ ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ እና ምስራቅ ሸዋ ዞኖች፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ ምዕራብ ሀረርጌ፤አዲስ አበባ፤ ድሬዳዋና ሀረሪ፣ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ




ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ጉራጌ፣ ሃዲያ፣ ሀላባ፣ ከምባታ፣ ስልጤ፣ የየም ዞኖች፣ ጠምባሮ፣ ቀቤና እና ማረቆ ልዩ ወረዳ፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዳውሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ቤንች ሸኮ፣ ኮንታ ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ወላይታ፣ ጎፋ፣ ጋሞ፣ ጌድኦ እና ባስኬቶ ዞኖች፤ በሲዳማ ክልል ዞኖች በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 6 እና 7)፡፡

በሌላ በኩል ከዕለት ወደ ዕለት ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት ከኦሮሚያ ክልል የባሌ እና ምስራቅ ባሌ ሰሜናዊው ክፍል፣ ምስራቅ ሀረርጌ፣ ጉጂ እና ምዕራብ ጉጂ ዞኖች፤ ከሱማሌ ክልል ሲቲ፣ ፋፋን፣ ጀራር፣ ኤረር እና ኖጎብ፣ ዞኖች፤ ከአፋር ክልል አዉሲ እና ማሂ ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ኮንሶ፣ አሪ ደራሼ፣ አማሮ ፣ ቡረጂ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች እንዲሁም ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ምዕራብ ኦሞ ዞን ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 6) ፡፡




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከኦገስት 1-10, 2024 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከኦገስት 1-10, 2024 የሚኖረዉ ከፍተኛ የዝናብ መጠን




ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

## ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

### እ.ኤ.አ ከኦገስት 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

በመደበኛ ሁኔታ በኦገስት ሁለተኛዉ አስር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ከቀዳሚው አሥር ቀናት በበለጠ ሁኔታ እየተጠናከሩ የሚሄዱበት ጊዜ ነው፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች በአንዳንድ ቦታዎች ላይ በረዶ የቀላቀለ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ለወንዞች ሙላትና ለቅጽበታዊ ጎርፍ መከሰት አስተዋጽኦ ያደርጋሉ፡፡ በአጠቃላይ በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች አንጻራዊ መጠናከር ሊኖራቸው እንደሚችል ይጠበቃል፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ በተለያዩ የሀገሪቱ ሥፍራዎች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከፍተኛ መጠን ያለው ዝናብ ሊመዘገብ እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በመሆኑም በመጪዎቹ የኦገስት ሁለተኛዉ አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በአብዛኛዎቹ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ በተስፋፋና በተጠናከረ ሁኔታ ቀጣይነት የሚኖረው ሲሆን፤ በተለይም በምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ሰሜን፣ ሰሜን ምስራቅና እና የመካከለኛዉ የሀገሪቱ አካባቢዎች የተሻለ የዝናብ መጠንና ስርጭት እንደሚኖራቸው አሀዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ (ካርታ 8)፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች የተነሳ በተለይም በሰሜንና በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ስፍራዎች ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖር አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 8) ፡፡




ካርታ 8 እ.ኤ.አ ከኦገስት 11-20_2024

የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አስር ቀናት የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የሚጠበቀው እርጥበት ለመኸር የግብርና ስራ እንቅስቃሴ የጎላ ጠቀሜታ እንደሚኖረውና አስቀድመው ተዘርተው በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የረጅምና የመካከለኛ ጊዜ ሰብሎች ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም ለቋሚ ተክሎች፣ ለጓሮ አትክልቶችና ፍራፍሬዎች የውሃ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም በደቡብ ኦጋማሽ፣ በምስራቅ እና በሰሜን ምስራቅ ለሚገኙት አርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል የጎላ ጠቀሜታ ይኖረዋል። በአንጻሩ በአንዳንድ ቦታዎች በሚኖረው ተደጋጋሚ የሆነ የእርጥበት ሁኔታ ጋር ተያይዞ የውሃ በማሳ ላይ መተኛት፣ ተዳፋታማ በሆኑ አካባቢዎች ደግሞ የመሬት መንሸራተት፣ በጎርፍ የመጠቃት እንዲሁም እርጥበት በሚበዛባቸው አካባቢዎች ለሰብል በሽታ መከሰት እና የአረም መስፋፋት ሊያስከትል ይችላል፡፡ በመሆኑም አርሶ አደሮችና የሚመለከታቸው አካላት የጎርፍ መቀልበሻ ቦዮችን ማዘጋጀት፣ የማንጣፈፍና የመከላከል ስራ በመስራት፤ እንዲሁም የፀረ-አረም እና ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ለመጠቀም የአየር ሁኔታ ምቹነትን ባገናዘበ ሁኔታ ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አስር ቀናት አባይ፣ ተከዜ፣ አዋሽ፣ ባሮአኮቦ፣ ኦሞጊቤ፣ አፋር ደናክል፣ የላይኛው እና የመካከለኛው የስምጥ ሸለቆ፣ ዋቤ ሸበሌ እና የገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ የእርጥበት ሁኔታ ይኖራቸዋል፡፡ ይህም የእርጥበት ሁኔታ የገጸ ምድር እና የከርሰ ምድር ውኃን ከማሻሻል እንዲሁም የግድቦችን እና የወንዞች የውኃ መጠን



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ከማኅልበት አንጻር አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል። በሌላ በኩል በተለይም በላይኛው እና የመካከለኛው ተከዜ፣ አዋሽ፣ ኦሞጊቤ፣ አፋር ደናክል፣ እንዲሁም በአባይ ተፋሰሶች ላይ ሊኖር ከሚችለው በጣም እጅግ ከፍተኛ የእርጥበት ሁኔታ ጋር ተያይዞ የቅጽበታዊ ጎርፍ፣ የወንዝ ዳርቻዎች በውኃ የመጥለቅለቅ ክስተቶች በተለይም ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ የከተማም ሆነ የገጠር አካባቢዎች ላይ ሊከሰቱና በህይወት፣ በንብረትም ሆነ በመሰረተ ልማት ላይ ጉዳት ሊያስከትል ስለሚችል ማህበረሰቡና የሚመለከታቸው አካላት የጎርፍ ማፋሰሻዎች ማፅዳት፣ የወንዝ ዳርቻዎችን መገደብና እንዲሁም ግድቦች እና የተለያዩ የውሃ መጠራቀምያዎችን በቅርበት መቆጣጠርና ክትትል ያስፈልጋል። በተጨማሪም ለመሬት መንሸራተት አደጋ ተጋላጭ የሆኑ አካባቢዎች ማህበረሰቡ ተገቢውን ጥንቃቄ በማድረግ ተያያዥ አደጋዎችን ለመቀነስም ሆነ ለማስቀረት የሚያስችሉ ተግባራትን ማከናወን ያስፈላጋል፡፡



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et